# የACPS Express 10/7/2022: የ‘ሱፐ ስፖትላይት (Supe’s Spotlight)’: የኦክቶበር (October) የቪዲዮ መልዕክት

## የ‘ሱፐ ስፖትላይት (Supe’s Spotlight)’: የኦክቶበር (October) የቪዲዮ መልዕክት




የ[ኦክቶበር (October) የ‘ሱፐ ስፖትላይት (Supe’s Spotlight)’ - ከACPS ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ - ከዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt) ጋር] በመሆን፣ የ‘Hispanic Heritage’ ወርን አክብሯል። በተጨማሪም፤ ዶ/ር ኬይ-ዋየት (Dr. Kay-Wyatt)፣ ከACPS ማህበረሰብ ጋር በመሆን — በአንድነት-ሆነን ስኬታማነት ላይ ሊያደርሰን ስለሚችሉ ነገሮች በጉጉት ወደፊት እየተመለከቱ ያላቸውን ፍላጎት አንጸባርቀዋል።

## ለብሄራዊ የ‘Hispanic Heritage’ ወር - የተማሪ አጉልቶ-ማሳያ (Spotlight) የሆነው: ‘Latinos Unidos’




‘Latinos Unidos’ ዓላማ-አድርጎ ተቀርጾ-የነበረው - በCOVID-19 ወረርሽኝ ወቅት በ2021-22 የትምህርት ዓመት ላይ፣ መስራቹ የሆኑት ፕሬዚዳንት ሲትላሊ ቻምበርስ ( President Citlali Chambers) - የክለቡ የላቲን ተማሪዎችን በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ውስጥ ኃይል-እንዲኖራቸው ያለውን አስፈላጊነት በመመልከት የተመሰረተ-ነበር። አሁን የACHS ሲኒየር (senior)፤ ቻምበርስ (Chambers) እንዳሉት፤ የላቲን ተማሪዎች - ለእነርሱ ግድ-በሚላቸው ጉዳዮች ላይ ለመነጋገር እንዲችሉ፤ ይህ መድረክ አስፈልጎ እንደነበር ተናግረዋል። “የእኛ ክለብ፣

በተጨማሪም - ከተመሳሳይ የቀደመ-መነሻ (backgrounds) እና የባህል ተሞኮርዎች ጋር የሚገኙ ተማሪዎችን እንደ-አንድ የደህንነት ስፍራ (safe space) አድርጎ የሚያገለግልም ነው፣” ብለዋል ቻምበርስ (Chambers)።

የላቲኖ ባህል በጣም ቆንጆ እና በቀላሉ-የማይሰበር (resilient) ነው፣ እና በጭራሽ እንደ-ተራ ነገር መወሰድ-የለበትም፤ ብለው ገልጸዋል ቻምበርስ (Chambers)፤ እና ‘Latinos Unidos’ ተገቢ-የሆነውን አክብሮች እና እውቅናን እንዲያገኝ ለማረጋገጥ ረድቷል። እንደ-ምሳሌ በማቅረብ - ሲናገሩ፤ ከለቡ - የላቲን ባህል ቆንጆ እንደሆነ ለማሳየት - በዚህ ወር ብቻ ሳይሆን በዓመቱ ሙሉ፣ በአሌክሳንድርያ ማህበረሰብ ውስጥ አድናቆትን-እንዲያገኝ ለማድረግ - በርካታ ዝግጅቶችን፣ በብሄራዊ የ‘Hispanic Heritage’ ወር ላይ በማዘጋጀት፣ ትልቅ-ሚና ሲጫወት ቆይቷል፤ ብለዋል። ቻምበርስ (Chambers) በተጨማሪ የሚያምኑት - የላቲን ባህል ዋጋ-የሚሰጠው - ጠንክሮ-በመስራት እና በአክብሮት - በ‘STEM’፣ በአትሌቲክስ ወይም በታዳሚ-ፊት የሚቀርቡ ስነጥበባት (performing arts) - በየትኛውም-ቢሆን፣ ተማሪዎችን በACHS ውስጥ ያላቸውን አጠቃላይ-ተሞክሮ ማበልጸግ ላይ ነው። ባለሁለት-ቋንቋ ተናጋሪ መሆን እና የበርካታ-ባህሎች ተሞክሮዎች መኖር፤ ሰዎችን የበለጠ ለሌሎች ባህሎች አድናቆት-ሰጪ እንዲሆኑ እና የተሻለ ግንኙነቶችን ከራሳቸው ጋር ለመፍጠር የሚረዳቸው ሆኖ እንደሚሰማቸው ገልጸዋል።

የ‘Latinos Unidos’ የተቋም ስፖንሰር የሆኑት ሌስሊ አውሴዳ (Leslie Auceda) ሃሳባቸውን-ሲያጋሩ - በ1990ዎቹ ውስጥ በማውንት ቨርነን ኮሚውኒቲ (Mount Vernon Community) ትምህርት ቤት ውስጥ በሚማሩ-ጊዜ፣ በክፍል-ውስጥ ስፓኒሽ መናገር አይፈቀድም ነበር - በማለት አጋርተዋል። “አሁን፣ ባለሁለት ቋንቋ ተናጋሪነት (bilingualism) ዋና-የሆነ ዋጋ ያለው ነው፣” ብለዋል አውሴዳ (Auceda)።  በመጨመርም-ሲናገሩ፤ ለስደተኞች ተማሪዎች - የስፓኒሽ ቋንቋን መማራቸው ጠቃሚ-እንደሆነ እና፤ አንዳንድ ቤተሰቦች ልጆቻቸው - ከሌሎች ጋር ለመዋሃድ እንዲያስችላቸው እና እነርሱ-የገጠማቸውን ዓይነት ዘረኝነት እንዳይደርስባቸው ሲሉ -  ስፓኒሽ-ቋንቋን ከመናገር እንዲቆጠቡ ሊያደርጓቸው ይችላሉ።

ቻምበርስ (Chambers) የባለሁለት ቋንቋ ተናጋሪነት ላይ የሚሰማውን ኩራት ሲመለከቱት፤ የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት-እና የፀረ-አፓርታይድ አክቲቪስት የነበሩት ኔልሰን ማንዴላ (Nelson Mandel) - የተናገሩትን በመጥቀስ፤ “ለአንድ-ሰው በሚገነዘበው-ቋንቋ ካነጋገራችሁት፣ ወደ ጭንቅላቱ ይገባል። በራሱ ቋንቋ ብታናግሩት፤ ወደ ልቡ-ዘልቆ ይገባል”። በደንበኞች አገልግሎት (customer service) ውስጥ በሚሰሩበት ጊዜ ከገጠማቸው የራሳቸው ተሞክሮ ጋር በማገናኘት፤ ስፓኒሽ-እንደምናገር ደንበኞች ሲያውቁ - ፊታቸው በደስታ ይፈካ መመልከት ያስደስታቸው እንደነበር - ቻምበርስ (Chambers) አሳውቀዋል። እርሳቸው-እንዳስቀመጡት፤ “ከሰዎች ጋር በመጀመሪያ-ቋንቋቸው ከመነጋገር የሚመጣው ይህ ጥልቅ-የሆነ ግንኙነት፣ ባለሁለት-ቋንቋ ተናጋሪ ከመሆን የሚገኝ በእርግጥ ግሩም-የሆነ ጥቅሙ ነው።” ብለዋል።

ከትምህርት-በኋላ የሚሰበሰበው - ‘Latinos Unidos’፣ ሁሉንም ተማሪዎች የሚቀበል-ነው። ቻምበርስ (Chambers) ጨምረው-ሲገልጹ፤ ከለቡ አንዳንድ ላቲኖ-ያልሆኑ አባላቶች የተቀላቀሉ ያሉበት እና፣ ይህ የሆነበትም ምክንያት የላቲኖ ማህበረሰብን በACHS ውስጥ ለመደገፍ ስለሚፈልጉ እና ስለዚህ ጠንካራና-ህያው የሆነ ባህል የበለጠ ለማወቅ ስለሚፈልጉ ነው።

# እጩዎች፣ እንዲቀርቡ መጠየቅ: የዓመቱ ምርጥ ርዕሰ-መምህር እና አስተማሪ፣ ሽልማቶች



በእያንዳንዱ ዓመት፤ ACPS - በ'The Washington Post' ላይ፣ [የዓመቱ ምርጥ ርዕሰ መምህር እና የዓመቱ ምርጥ አስተማሪ ሽልማቶች]፤ በክልሉ የትምህርት አሰጣጥ ብልጫ ያመጡትን እውቅና በመስጠት ላይ ይካፈላል። ሁሉም የACPS ማህበረሰብ አባላቶች፤ — ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና የአሌክሳንድርያ ነዋሪዎችን ጨምሮ— ከዚህ በታች በተዘረዘረው መስፈርት መሠረት - የእጩ-ምርጫቸውን እስከ ኦክቶበር (Oct.) 24 ቀን 2022 እንዲያደርጉ ይጋበዛሉ:

- አስተማሪን ለእጩነት ለማቅረብ፤ ከኦክቶበር (Oct.) 24 ቀን 2022 በፊት፣ ወደ ርዕሰ መምህሩ የጽሁፍ-መግለጫ ላኩ። እያንዳንዱ ርዕሰ መምህር - ከሠራተኞች ጋር ኢጋርነትን በመፍጠር፤ አንድ-እጩ - ከየትምህርት ቤቶቻቸው በመምረጥ ወደ ACPS የመጨረሻ ዙር እንዲያልፉ ያደርጋሉ።
- ርዕሰ መምህርን ለእጩነት ለማቅረብ፤ ወደ ሼሪ ቱሊአ (Sherri Tullia)፣ የመማር እና የአመራርነት መምሪያ (Department of Teaching, Learning and Leadership) ወደሆኑት፤ በsherri.tullia@acps.k12.va.us እስከ ኦክቶበር (Oct.) 24 ቀን 2022 ድረስ፣ እባካችሁ መግለጫ ላኩ።

ለ'Washington Post' የዓመቱ ምርጥ አስተማሪ ሽልማት፣ ብቁ ለመሆን፤ እጩ-የሚሆኑት የሙሉ-ሰዓት (full-time) አስተማሪ መሆን (ከቅድመ-መዋዕለሕፃናት እስከ 12ኛ)፤ እና እንደ ጋዜጣው ዝርዝር ግዛቶች መሠረት፤ እውቅናን-ካገኘ የዋሽንግተን ሜትሮ-አካባቢ ክልልው ውስጥ ከሚገኝ ትምህርት ቤት ውስጥ መሆን አለባቸው። እጩዎቹ፤ እንደ አስተማሪነት ቢያንስ የ5 ዓመታት ልምድ ያላቸው፤ ከእነዚህም ዓመታት ውስጥ ሦስቱ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም አሁን በሚያገለግሉበት የትምህርት ቤት ስርዓት ውስጥ መሆን አለበት።

እጩዎቹ፤ ለ2022-23 የትምህርት ዓመት በአስተማሪነት ማገልገል ያለባቸው እና የሚከተሉትንም መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው:

- በተማሪዎች ውስጥ የመማር እና ስኬታማ-የሆን ፍላጎትን መትከል የሚችሉ።
- እያንዳንዱ ተማሪዎች የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች መገንዘብ የሚችሉ፣ ተሰጥያአቸውን የሚያበረታቱ እና በራስ-መተማመናቸውን የሚያበለጽጉ።
- በትምህርት ዓይነቱ ዝርዝር ውስጥ ብቃት-ያለው እውቀትን የሚያሳዩ እና ይህንኑም ከተማሪዎች ጋር በተሳካ-ሁኔታ ማጋራት የሚችሉ።
- ከስራ-ባልደረቦቻቸው ጋር እና ከማህበረሰቡ ጋር፣ ትብብርን የሚያሳድጉ።
- የላቀ-አመራርን የሚያሳዩ።
- በ2022-23 የትምህርት ዓመት ውስጥ፤ የማስተማር የስራ-ምድብ ሆነውን የስራ-ድርሻቸውን የጠበቁ።

ለ'Washington Post' የዓመቱ ምርጥ ርዕሰ መምህር ሽልማት፣ ብቁ ለመሆን፤ እጩ-የሚሆኑት የሙሉ-ሰዓት (full-time) ርዕሰ መምህራን መሆን (ከቅድመ-መዋዕለሕፃናት እስከ 12ኛ)፤ እና እንደ ጋዜጣው ዝርዝር ግዛቶች መሠረት፤ እውቅናን-ካገኘ የዋሽንግተን ሜትሮ-አካባቢ ክልልው ውስጥ ከሚገኝ ትምህርት ቤት ውስጥ መሆን አለባቸው። እጩዎቹ፤ እንደ ርዕሰ መምህርነት ቢያንስ - የ5 ዓመታት ልምድ ያላቸው፤ ከእነዚህም ዓመታት ውስጥ ሦስቱ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም አሁን በሚያገለግሉበት የትምህርት ቤት ስርዓት ውስጥ፤ ያላቸው መሆን አለበት።

እጩዎቹ፤ ለ2022-23 የትምህርት ዓመት በአስተዳደርነት ማገልገል ያለባቸው እና የሚከተሉትንም መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው:

- በብቃት ማስተዳደር የሚችሉ።
- የፈጠራ-አስተሳሰብ እና ፈጠራዊ-ስራን የሚያበረታቱ እና የሚያሳዩ።
- በትምህርት ቤት እና በማህበረሰቡ መካከል ትብብርን የሚያሳድጉ።
- በተማሪዎች እና በወላጆች መካከል እንዲሁም በተቋሙ እና በሠራተኛው መካከል፣ ቀጣይነት ያለው ውይይትን የሚያስጠብቁ።
- በትምህርት አሰጣጥ መስኮች ውስጥ፣ ዘላቂነት ያለው እድገቶችን የሚጠብቁ።
- የቡድናዊ-አሰራር እንዲኖር የሚያበረታቱ።
- አመራርነትን የሚያሳዩ እና ትጋትን በምሳሌነት የሚያሳዩ።
- በመማሪያ-ክፍል ውስጥ፣ ቀጣይነት ያለው ንቁ ሚናን የሚጫወቱ።
- በ2022-23 የትምህርት ዓመት ውስጥ፤ እንደ ርዕሰ መምህር ሆነው የስራ-ድርሻቸውን የጠበቁ።

የACPS የዓመቱ ምርጥ ርዕሰ መምህር እና የዓመቱ ምርጥ አስተማሪ፤ በACPS ፓናል (panel) አማካኝነት፣ በ2023 መጀመሪያ ላይ የሚመረጡ እና በኤፕሪል (April) 2022 ላይ ደግሞ ማንነታቸው የሚገለጽ ይሆናል። ለ'The Washington Post ሽልማቶች'፣ እንደ ወደ የመጨረሻ-ዙር የደረሱ ሆነው፤ አሸናፊዎቹን በኤፕሪል (April) ወር 2023 ውስጥ ይታወቃሉ።

## የ'SLEP' የዳሰሳ-ጥናት: የማብቂያው-ቀን፣ ወደ ኦክቶበር (Oct.) 9 ቀን 2022 ተራዝሟል



የዚህ የዳሰሳ-ጥናት የማብቂያው-ቀን፣ ተራዝሟል! ያላችሁን አስተያየት (feedback)፣ በ'School + Law Enforcement Partnership (SLEP) የዳሰሳ-ጥናት አማካኝነት እስከ እሁድ ኦክቶበር (Oct.) 9 ቀን - በ11:59 p.m. ድረስ - እባካችሁ-አስገቡ። የዳሰሳ-ጥናቱ፤ ለቤተሰቦች፣ ሠራተኞች፣ እና ከ6-12 ክፍል ላሉ ተማሪዎች ለማጠናቀቅ ከ10-15 ደቂቃዎችን የሚወስድ እና፣ ከ'SLEP Advisory Group' ጋር ስለ ትምህርት ቤት ደህንነት እና ጥበቃ አብሮ ለመስራት-ወሳኝ ነገር ነው።

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools '(ACPS) ዋና-እሴቶቹ አድርጎ ያካተተው፤ ትምህርት ቤታችን ሁሉን የሚቀበል መሆኑን፣ እና ለሁሉም ሰው በደህንነት ተገኝቶ-የሚማርበት መሆኑን ማረጋገጥ ነው። ከዚህ የዳሰሳ-ጥናት የተገኙ ውጤቶች፤ የ'SLEP Advisory Group'ን፤ በመጪው በዲሴምበር (December) 2022 - በACPS እና በአሌክሳንድርያ የፖሊስ መምሪያ  መካከል እንደገና-እንዲታሰብ በታቀደው ኢጋርነት፣ ለትምህርት ቤት ቦርዱ ያቀረበውን የአስተያየት-ሃሳቦች ላይ፣ በቀጥታ ለመጠቀም ጥቅም-ላይ ይውላል። በተጨማሪም፤ የዳሰሳ-ጥናት ምላሽ-ሰጪዎች፣ በመጪው የ'focus group' ውይይቶች ላይ - ስለ ትምህርት ቤት እና ክፍሉ (division) ደህንነት እና ጥበቃ ላይ፣ ተካፋይ-የመሆን ፍላጎት እንዳላቸው የሚጠቁም ይሆናል።

ስለ 'SLEP Advisory Group'፣ ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፤ እባካችሁ የACPS ድህረ-ገጽን ጎብኙ።

# የ‘Lyles Brothers’ን ክብር-ለመስጠት በኦክቶበር (Oct.) 10 ቀን 2022 - እውቅና-መስጫ ክብረ-በዓል




የአሌክሳንድርያ ከተማ፤ ከዚህ ቀደም በ2016 እውቅና-ያገኘው፣ በቀድሞው ቲ.ሲ ዊሊያምስ (T.C. Williams) ትምህርት ቤት (አሁን- የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት የሆነው) በተመራቂዎች የሩጫ እና ሜዳ ሻምፒዮናዎች ኖሃ እና ዮሲፈስ ላየልስ (Noah and Josephus Lyles)ን በኦክቶበር (Oct.) 10 ቀን 2022 ላይ በ6:15 p.m. ላይ በ‘City Hall Market Square’ (301 King Street) በሚደረገው እውቅና-መስጫ ክብረ-በዓል ላይ ይከናወናል። ሁለቱ ቲታን (Titan) ተመራቂዎች፤ በከፍተኛ-ደረጃ ያለው ብቃት የ‘ሩጫ ሜዳን/track and field’ን ያጠናቀቁ እና እንደ የላቀ-ደረጃን ያስመዘገቡ የማህበረሰብ አምባሳደሮችም ሆነው አገልግለዋል። በቅዳሜ ዕለት፣ አክቶበር (Oct) 8 ቀን 2022 ላይ፣ ወደ አሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)- የ2022 የአትሌቲክ/Athletic ‘Hall of Fame’ የሚተዋወቁ-ይሆናል።

በዚህ ሰኞ በሚካሄደው የእውቅና-መስጫ ክብረ-በዓል ላይ፤ የአሌክሳንድርያ ከንቲባ ጀስቲን ዊልሰን (Mayor Justin Wilson) አዋጁ/proclamationን የሚያነቡ ይሆናል። ኖሃ ላየልስ (Noah Lyles)፣ የ2020 የኦሎምፒክ የመዳብ/bronze ተሸላሚ እና በ200-ሜትር በዓለም የአትሌቲክስ ሻምፒዮናነት - የአሜሪካ ሪከርድን የያዘው፤ የአሌክሳንድርያ ከተማን - ቁልፍ (key) የሚሸለም-ይሆናል።

ሌሎች ተጋባዥ ንግግር-ለማድረግ ወደ ዝግጅቱ የሚካተቱት፤ የአሌክሳንድርያ ትምህርት ቤት ቦርድ ሊቀ-መንበር - ሜጋን አልደርተን (Meagan L. Alderton)፣ የACPS ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt) እና የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ርዕሰ መምህር - ፒተር ባላስ (Peter Balas) - ናቸው።

## በኦክቶበር (Oct.) 12 ቀን 2022 ላይ፣ ወደ ትምህርት ቤት ቀኑ - ‘Walk & Roll’ን ለማክበር፤ ተዘጋጁ




የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - የ26ተኛውን ዓመታዊ ብሄራዊ ወደ ትምህርት ቤት ቀኑ - በእግር-መሄድ እና በተሽከርካሪ (Walk and Roll) ላይ - ሮብ፣ ኦክቶበር (Oct.) 12 ቀን 2022 ላይ አብራችሁ ለመካፈል፤ የጫማችሁን ክሮች-በማሰር የምትሰናዱበት ጊዜ ነው። የአሌክሳንድርያ ከተማ - የመጓጓዣ እና የአካባቢያዊ አገልግሎቶች (Transportation and Environmental Services) - ከACPS ጋር በመተባበር፣ ዝግጅቱን ለማበረታታት፣ በርካታ የእግር-ጉዞዎችን እና የብስክሌት መንዳትን፤ ለናኦሚ ኤል. ብሩክስ (Naomi L. Brooks) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ቤተሰቦች - የማበረታቻ አጭር ቪዲዮን አቅርቧል።

ሁሉም የትምህርት ቤት ክፍል/division - በዚህ ዝግጅት ለመካፈል የተመዘገቡ ሲሆን ይህም - ለተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት በእግር-በሚጓዙ እና በሚያሽከረክሩ ጊዜ - የደህንነት-ጥበቃን ለማበረታታት ነው። እንደዚህ ያሉ ዝግጅቶች፤ ተማሪዎች የበለጠ ንቁ-እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ እያበረታታ-እያለ፤ ጎን-ለጎን ደግሞ - ወደ ትምህርት ቤት መሄጃ መንገዶችን ደህንነቱ-የተጠበቀ እንዲሆን መፍትሄዎችን በመፈለግ፣ ማህበረሰቡን ለመርዳት ነው።

ለትምህርት ቀኑ ለ’Walk and Roll’ የተዘጋጀውን የማስታወቂያ በራሪ-ወረቀቶችን - በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ ወይም በአረብኛ ማግኘት-ይቻላል።

## ቀኑን-አስታውሱ፤ እዳትረሱት: ‘PTAC’፣ ‘PSAS’ እና ‘ACPS’፣ የሕዝብ ደህንነት ጥበቃ ፎረም - በኦክቶበር (Oct.) 26 ቀን 2022 እንዲደረግ፣ ተዘጋጅቷል



በኦክቶበር (Oct.) 26 ቀን 2022 ላይ፣ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፣ የአሌክሳንድርያ የፒቲኤ (PTA) ካውንስል (PTAC) እና የወላጆች ለደህንነት በአሌክሳንድርያ ትምህርት ቤቶች (Parents for

Safe Alexandria Schools (PSAS) - ሁሉም በጋራ - የትምህርት ቤት ደህንነት ፎረምን ለACPS ማህበረሰብ አዘጋጅተዋል። በዚህ ፎረም ወቅት፤ ተሳታፊዎች ስለ ተማሪዎቻችንን እና ሠራተኞችን በደህንነት ስለመጠበቅ እንዲረዳ - ሁላችንም ምን ማድረግ እንዳለብን ለፓናል የማህበረሰብ ባለሞያተኞች ጥያቄ ለማቅረብ ዕድል ይሰጣል።

ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ የሆኑት - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)፤ በትምህርት ቤቶቻችን እና በማህበረሰባችን ውስጥ፣ የደህንነት-ጥበቃን ጠብቆ-በመገኘት ላይ - የክፍሉ/divisionን - ከአሌክሳንድርያ ፖሊስ መምሪያ (Alexandria Police Department (APD) ጋር የሚያደርገውን ትብብር፣ እና በዚህ የጋራ-በሆነ ዓላማ ላይ ቤተሰቦች ከACPS-ጋር እንዴት እንደሚሠሩ፤ ንግግር-ያደርጋሉ። ልጅ-ቢሰማው አስቸጋሪ-ሊሆን የሚችል (Child-sensitive) ይዘት፤ ውይይት-እንደሚደረግበት፤ እባካችሁ አስታውሱ። የፎረሙ ፓናሊስቶች (Panelists) ሆነው የተካተቱት:

- የACPS የደህንነት እና የጥበቃ አገልግሎቶች (Safety & Security Services) ዳይሬክተር — ጆን ኬንትሬራስ (John Contreras)።
- የACPS የትምህርት ቤት የማህበራዊ ስራ ዳይሬክተር — ፋይዛ ጃክሰን (Faiza Jackson)።
- የአሌክሳንድሪያ የፖሊስ መምሪያ ሹም — ሪቻርድ ሳንዳቮል (Richard Sandavol)።
- የአሌክሳንድርያ ከተማ የወንበዴ-ቡድን (Gang) መከላከያ የማህበረሰብ ታስክ-ፎርስ (Task Force) አባል — ማይክ ማኪይ (Mike Mackey)።
- የ'Be SMART' የጦር-መሣሪያ (Gun) በጥብቅ-ቦታ ማስቀመጥ (Secure Gun Storage) ፕሮግራም፤ የእያንዳዱ-ከተማ የጦር-መሣሪያ (Gun) የደህንነት-ጥበቃ — አንዲ ኮርሶ (Andy Corso)።
- የአሌክሳንድርያ ከተማ፣ የመጓጓዣመምሪያ (Department of Transportation) & የአካባቢያዊ አገልግሎቶች (Environmental Services) — አሌክስ ካሮል (Alex Carroll)።

የትምህርት ቤት የደህንነት-ጥበቃ ፎረም፣ በጆርጅ ዋሽንግተን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት - የመሰብሰቢያ-አዳራሽ ውስጥ፣ ከ6:30 እስከ 8 p.m ድረስ ይካሄዳል። ፒዛ (Pizza)ም፣ ይቀርባል። በhttps://acps.cc/SafetyForum ላይ፣ ቤተሰቦች መገኘታቸውን-እንዲያረጋግጡልን (RSVP እንዲያደርጉ) እንጠይቃለን። መላው-ሕዝቡም፣ በዙም (Zoom) አማካኝነት፣ በhttps://acps.cc/psfonzoom ላይ - በደህንነት-ጥበቃው ፎረም ላይ መካፈል ይችላሉ።
የማስተርጎም አገልግሎቶች፤ በአማርኛ፣ በአረብኛ፣ በዳሪ፣ እና በስፓኒሽ ቋንቋዎች - ለሁለቱም በአካል-ተገኝቶ ለሚደረገው እና ለርቀት (virtual) ዝግጅቶቹ - መገኘት የሚችል-ይሆናል። ተጨማሪ-ለማወቅ - የየዝግጅቱን ድህረ-ገጽ በመጎብኘት፤ ወይም ተለጣፊ-ማስታወቂያዎቹን፤ በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽ፣ በዳሪ፣ በአማርኛ ወይም በአረብኛ በመመልከት-ማወቅ ይቻላል።

## በ'ቀይ-ሪባን ሣምንት (Red Ribbon Week) የፖስተር ውድድር ውስጥ፤ ለማሸነፍ ተሳተፉ




በሕይወት-መኖርን፤ በምስጋና ማክበር። የዕፅ ነፃ-የሆነ ሕይወት።™ ይህን ዝግጅት ከኦክቶበር (Oct.) 23-31 ድረስ እውቅና-በምንሰጥበት ጊዜ፤ ይህ - የ2022 የብሄራዊ የቀይ-ሪባን ሣምንት (Red Ribbon Week) መለያ-ገጽታው (theme) ነው። ሁሉም የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ተማሪዎች በሙሉ፣ ከዕፅ-ነፃ

የሆነ የአናኗር-ዘዴን ለማበረታታት እንዲረዳ፣ በቀይ-ሪባን የፖስተር ውድድር (Red Ribbon poster contest) ውስጥ እንዲካፈሉ ተጋብዘዋል።

ሦስት የማስገቢያ ምድቦች አሉት: የመጀመሪያ ደረጃ፣ መካከለኛ ደረጃ እና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት። ሁሉም ፖስተሮች እስከ ኖቬምበር (Nov.) 15 ቀን 2022 መግባት እና ፖስታ-የተላከበት ምልክት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል እና ወደሚከተለው መላክ አለባቸው:

ሚስ ዳኒኤላ ፔሬዝ-ብራቮ (Ms. Daniela Perez-Bravo)
ACPS Central Office
1340 Braddock Pl, 5th Floor,
Alexandria, VA 22214

የኤሌክትሮኒክ ስሪቶቹ (Electronic versions)፤ ወደ face@acps.k12.va.us ወይም በwww.acps.cc/RRWposter22 ሊገቡ-ይችላሉ።

ከዕፅ-ነፃ የሆነ የአናኗር-ዘዴን የሚያበረታታ፤ በሰዓሊነት አቀራረብ እና በጠንካራ መልዕክት አቅራቢነታቸው ላይ መሠረት አድርጎ፤ ሦስት አሸናፊ የሆኑ ፖስተሮች ይመረጣሉ። የ'Red Ribbon poster' ውድድር አሸናፊዎች፤ እያንዳንዳቸው የ$100 የስጦታ ካርድ (gift card) የሚያገኙ፣ እና የሰሩትም ፖስተሮች - በ2023 የቀይ-ሪባን ሣምንት (Red Ribbon Week) ወቅት-ውስጥ እንዲታይላቸው ይደረጋል።

የ'ቀይ-ሪባን ዘመቻ (The Red Ribbon campaign)'፤ በሃገሩ ውስጥ ለረጅም-ጊዜያት ሲያገለግል የነበረ እና ትልቁ የዕፅ መከላከያ ፕሮግራም ነው። ከአሌክሳንድርያ የአደንዛዥ-ዕፅ አለአግባብ መጠቀም መከላከያ ቅንጅት (Substance Abuse Prevention Coalition of Alexandria)፣ ከአሌክሳንድርያ ከተማ የማህበረሰብ እና የሰብ አዓዊነት አገልግሎቶች መምሪያ (City of Alexandria's Department of Community and Human Services)፣ የኖርዘን ቨርጅኒያ - የ'Stop Child Abuse Now'፣ እና ማንጓጠጥን-ጨርሶ ለማስቆም የከንቲባው ዘመቻ (Mayor's Campaign to End Bullying)፣ የACPS የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሣትፎ (ACPS Family and Community Engagement (FACE) ቡድን ጋር በአጋርነት በመስራት፤ ይህን-ዘመቻ መልሶ ወደ አሌክሳንድርያ በማምጣታቸው-ደስተኞች ናቸው። በሕይወት-መኖርን፤ በምስጋና ማክበር እና ከዕፅ ነፃ ሕይወት መኖር የሚለውን - ይዘን ወደፊት በምንገፋበት ጊዜ፤ ይህ ዘመቻ - ለማህበረሰቡ አብሮ-በአንድነት ለመቆም እና በጉልህ-በሚታይ ሁኔታ ዕፆችን በመቃወም በመቆም - ከታዳጊዎች ጋር ግንኙነትን መፍጠሪያ-ውጤታማ የሆነ መንገድ ነው።

## የኦክቶበር (Oct.) 6 ቀን 2022 - የትምህርት ቤት ቦርድ ማጠቃለያ



በዚህ ኦክቶበር (Oct.) 6 ቀን 2022 ስብሰባው ላይ፤ የትምህርት ቤት ቦርዱ፣ የሚከተሉትን ርዕሶች ላይ ተነጋግሮበታል:

- የMTSS/SEAL መዋቅር/structure።
- 'VDOE' እውቅና-መስጠት ላይ አዲስና-ማሻሻያ (update)።

- የተጣመረ የገንዘብ-እርዳታዎች (Combined Funds)ን በስራ-ላይ ማዋል እና የካፒታል ማሻሻያ ዕቅድ-አወጣጥ ቅድሚያ-የሚሰጠው በጀት።
- በትምህርት ቤት ወሰኖች (school zones) ዙሪያ፤ የ'15 mph' የመንጃ-ፍጥነትን ውሳኔ-መስጠት።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ [Electronic School Board]ን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በ[ትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ] መጎብኘት ትችላላችሁ።

## በሴፕቴምበር (Sept.) 29 ቀን 2022 - COVID-19 የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ሴፕቴምበር (Sept.) 29 ቀን 2022 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ በየ100,000 ሰዎች፣ 111.0 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ [Alexandria COVID-19 dashboard] ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በሴፕቴምበር (Sept.) 29 ቀን 2022 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቃላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ተመልክቷል።